በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 1
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Customs Commission No.1

ሰኔ 18 2014
6-3/0205/14

የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ:- <u>የእናት ጡት ወተትን የሚተኩና ለህፃናት የሚሆኑ Infant formulas ላልተወሰነ ጊዜ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ መሆናቸውን ስለመግለጽ፡፡</u>

የከገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/5646 በ14/10/2014 በተፃፈ ደብዳቤ የእናት ጡት ወተትን የሚተኩና በታሪፍ ቁጥር 1901.1000 የሚመደቡት Infant formulas ለህጻናት እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውንና አሁን ያለውን የገበያ ዋጋ ንረት ግምት ውስጥ በማስገባት በእንጥጥል ላይ ያሉ ጉዳዮችን ጨምሮ ላልተወሰነ ጊዜ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ሆነው እዲገቡ ተወስኗል፡፡

በመሆኑን ታሪፍ ቁጥር 1901.1000 በርካታ ለህጻናት የሚሆኑ ምግቦችን የሚያካትት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሆነውን Infant formulas ብቻ በመለየትና የተጨማሪ እሴት ታክስን ነፃ ለማድረግ በተዘጋጀው የጉምሩክ ፕሮሲጀር ኮድ /CPC/ በመጠቀም በውሳኔው መሰረት ተግባራዊ እንዲደገር እያሳሰብን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላለፈውን ደብዳቤ ቅጂ አንድ ገጽ አባሪ አድርገን ልከናል፡፡

በተጨማሪም በአገልግሎት አሠጣጥ ላይ ለጥንቃቄ ይረዳችሁ ዘንድ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሆኑት Infant formulas በውሀ ተበጥብጠው በቀጥታ የሚጠጡ ዝግጅቶች መሆናቸው እየገለጽን አስፈላጊ ከሆነም ከዚህ ደብዳቤ ጋር ለምሳሌ ተብለው አባሪ የተደረጉ እቃዎች አይነትና ተመሳሳዮች መሆናቸው ግንዛቤ ተወስዶ መስተንግዶ እንዲሰጥ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>:-

- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ፖሊሲ ጥናትና ትንተና ቡድን
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

